# የሶስተኛ ክፍል ትምህርት ሰሌዳ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በአንድ ደቂቃ ውስጥ በግራ እግርህ ምን ያህል ግዜ መዝለል ትችላለህ? በቀኝ እግርህስ? የዘለልከው ቁጥር በ <, >, ወይም = ተጠቅመህ አወዳድረው። ልዩነቱ ምን ያህል ነው? | ፍቃድ ጠይቀህ ለራስህ ለጓደኛህ ወይም ለቤተሰብህ አባል ጤነኛ መክሰስ ስራ። አሰራሩህን ፅፈህ ለክፍልህ ተማሪዎች ንገራቸው። | አንድ እንስሳ ስለህ ስለ እንስሳው ገጽታዎችና ባህርያት ጻፍ። እንስሳው ገጽታዎቹን ምን ለማድረግ ነው የሚጠቀምበት? እንስሳውን ተጠቅመህ የምግብ ሰንሰለት ሳል። | የምታነበውን መጽሓፍ ምረጥ። ካነበብ በኋላ ፈታኝ ሁኔታ ስለ አጋጠመው ገጸ ባህርይ ጻፍ። ስለ ፈታኙ ሁኔታ ገልጸህ ጻፍ፣ በምላሹ ገጸ ባህርይው ምን እንዳረገ ጻፍ። | ለ15 ደቂቃ ወይ ከዛ በላይ የሰውነት ማጎልመሻ ስራ። ፑሽ-አፕ፣ በጀርባህ ተኝተህ ከወገብ መነሳት፣ ቤት ውስጥ ዱብ ዱብ በል፣ የእግርህ ጣቶች መንካት፣ ኳስ ማንጠባጠብ ወይ በአንድ እግርህ መዝለል ትችላለህ። የትኛውን እንደ ሰራህ ጻፍ። |
| | እቤትህ ውስይ የሚኖሩ ሰዎችን የሁሉንም እድሜ ጻፍ። ድምሩ ስንት ሆነ። ከ100 ይበልጣል ወይስ ያንሳል? በምን ያህል? | ዛሬ ለእንድ ሰው ቢያንስ ሁለት የደግነት ተግባር አሳይ። ምን እንዳረክና እንደዛ ማድረግህ ምን ስሜት እንደ ፈጠረብህ ጻፍ። | ውሃ ከየት ማግኘት እንችላለህ? የወንዝ የሓይቅ የኩሬ የውቅያኖስ የከርሰ ምድር ውሃ እና የውሃ ጉድጓድ ስእል ሳል። | ጋዜጠኛ ሆነህ ስለ አንድ የመረጥከው ነገር ዜና ጻፍ። | የራስን ምስል መሳል። በመስታወት እያየህ የራስህ ምስል ሳል። በተቻለህ መጠን የምታያቸውን እያንዳንዱን ዝርዝር ገጽታ አካትት። |
| | በቅርቡ ያነበብከው ታሪክ ውስጥ ያሉትን ገጸ ባህርያት ተጠቅመህ መደመር መቀነስ ማባዛት ወይ ማካፍል የሚጠይቅ የሂሳብ ጥያቄ ፍጠር | አንድ የምትወደውን ሰው ወይ ባህል የሚያስታውስህ የምግብ አሰራር አንብብ። የምግብ አሰራሩ ምን እንደሆነና ልዩ የሚያደርገው ምን እንደ ሆነ ጻፍ። | ትነት በውሃ ዑደት ውስጥ፦<br><br>ሰማይ ላይ ደመና እንዴት እንደ ሚፈጠር በስእል አሳይ። ስእሉ ላይ እያንዳንዱን ሂደት ለይተህ ጻፍ። | መጽሓፍ አስተዋውቅ! ለጓደኛህ አንድ መጽሓፍ እንዲያነብ ሓሳብ አቅርብለት፣ ሌላን ሰው ምን መጽሓፍ እንድታነብ እንደ ሚመክርህ ጠይቅ። ምክንያቱን መግለጽ አትርሳ | ትልቅ ሰው እየረዳህ ጤነኛ መክሰስ ስራ። ምግቡን ጤነኛ የሆነው ለምን እንደሆነ ግለጽ። |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በቀን ውስጥ ሁለት የተለያየ ግዜ ላይ ሰዓት እይ። ትክክለኛውን ሰዓት መዝግብ። በእያንዳንዱ ሰዓት ላይ ምን እያረክ እንደ ነበር ወይ በስእል ወይ በጽሑፍ ግለጽ። | ለዘመድ ለጓደኛ ለወይ ጎረቤት ቃለ መጠይቅ አድርግ፣ ከዛም በዛ ሰው ህይወት የተከሰቱ ወሳኝ ክንውኖችን የሚያሳይ የግዜ ሰሌዳ ስራ። | የውሃ ዑደት የሚያሳይ ዲያግራም ሳል ወይ ሞዴል ስራ። ሃይል፣ ሙቀት፣ ትነት፣ ጥዘት እና ዝናብ የሚሉት ቃላት ተጠቅመህ ለትልቅ ሰው አስረዳ። | ለረጅም ግዜ ላላገኘህው ሰብ ደብዳቤ ጻፍ። በህይወትህ ውስጥ እየሆነ ስላለው ነገር ንገራቸው ስለ እነሱም ጠይቅ። | መጀመርያ ሰውነትህን አፍታታ። ከዛም ፑሽ-አፕ፣ በጀርባህ ተኝተህ ከወገብ መነሳት፣ (የትልቅ ሰው ፍቃድ ጠይቀህ) ከቤት ውጭ በእግርህ መሄድ የመሳሰሉትን ስፖርት ስራ። ሰውነት ማጎልመሻ ስራ። |
| | በቅርቡ ያነበብከው ታሪክ ውስጥ ያሉትን ገጸ ባህርያት ተጠቅመህ እስከ 1000 የመደመር ወይ የመቀነስ የሂሳብ ጥያቄ ፍጠር። | ለአንድ ሩቅ ቦታ የሚኖር ጓደኛ ወይ ዘመድ ደብዳቤ ጻፍ። እነሱን ልዩ ስለ ሚያደርጋቸው ነገር ጻፍ። | ፍቃድ ጠይቀህ አንድ ስለ አየር ሁኔታ የሚገልጽ ድህረ ገጽ እይ ወይም ጋዜጣ ላይ ስለ አየር ሁኔታ አንብብ። የዛሬውን የአየር ከነገው የአየር ትንበያ ጋር አወዳድር። | አንድ ደስ የሚል የንባብ ቦታ ፍጠር። ለአንድ አሻንጉሊት መጽሓፍ አንብብ፣ ስታነብ ምን እንደ ተሰማህ ለአሻንጉሊቱ ንገረው። | ከወላጅ/ጠባቂ/ ወንድም ወይ እህት/ጓደኛ ጋር ለአስር ደቂቃ በካልሲ ኳስ ሰርታቹ ቅብብሎሽ ተጫወቱ። |
| | የተለያዩ የማባዛት ታሪኮችን ተጠቅመህ መጽሓፍ ጻፍ ወይ በስእል ግለጽ | የደግነት የቀን መቁጠርያ ስራ። በሳምንቱ የደግነት ተግባሮች ለማሳየት አቅድ። የቀን መቁጠርያህ ለአስተማሪህ አሳይ። | ስለ አንድ ቀላል ማሽን መዝሙር ጻፍ ለምሳሌ ስለ ትንሽ ሹል ብረት፣ ጋሪና መጎተቻው። ከዛም ለሌላ ሰው ዘምርለት። | ድምጽ እየለዋወጥክ ተረት በምትተርትበት ድምጽ መጽሓፍ ማንበብ ተለማመድ። ስታነብ ወላህጅ በሞባይሉ ከቀዳህ የተቀዳውን ቪድዮ ለዘመድ ወይ ለጓደኛ ላክለት! | እጅህንና እግርህን ከመሬት ሳታነሳ እጅህን ወደ ኋላ አድርገህ ቤት ውስጥ ሶስት ግዜ ወደ ፊት ሂድ። ከዛም ሶስት ግዜ ወደ ኋላ ተመለስ። |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወደ አስርዮሽ ሲጠጋጋ፦<br><br>ወደ 50 ሊጠጋጋ የሚችል ትንሽ ሙሉ ቁጥር የቱ ነው? ወደ 50 ሊጠጋጋ የሚችል ትልቅ ሙሉ ቁጥር የቱ ነው? ስንት የተለያዩ ሙሉ ቁጥሮች ወደ 50 መጠጋጋት ይችላሉ? | በማሕበረሰብህ ውስጥ የሚሰጥ አገልግሎት ስለ ተጠቀምክበት ግዜ የሚገልጽ አንድ አንቀጽ ጻፍ። | በተፈጥሮ ውስጥ ማን ምን እንደ ሚበላ የሚያሳይ ቀላል የምግብ ሰንሰለት ሳል።.<br>🍀 → 🐇 → 🦊<br>የምግብ ሰንሰለት ላይ የሚታዩ ቀስቶቹ ኋይል እንዴት ከአትክልት ወደ እንስሳት እንደ ሚተላለፍ የሚያሳይ መሆን አለበት። | ስለ ምትወደው የቀለም ዓይነት ግጥም ጻፍ። ግምኡ ላይ ያንን ቀለም የሚያስታውሱህ ዕቃዎች፣ በታዎች ወይ ስሜቶች አካትት። | ከወላጅ/ጠባቂ/ ወንድም ወይ እህት/ጓደኛ ጋር ለአስር ደቂቃ በካልሲ ኳስ ሰርታቹ ቅብብሎሽ ተጫወቱ። |
| | ወደ መቶዎች ሲጠጋጋ፦ ወደ 500 ሊጠጋጋ የሚችል ትንሽ ሙሉ ቁጥር የቱ ነው? ወደ 500 ሊጠጋጋ የሚችል ትልቅ ሙሉ ቁጥር የቱ ነው? ስንት የተለያዩ ሙሉ ቁጥሮች ወደ 500 መጠጋጋት ይችላሉ? | 3 የሚያስፈልጉህን ነገሮችና 3 የምትፈልጋቸውን ነገሮች ጻፍ። ስለ አንድ የሚያስፈልግህ ነገር እና አንድ የምትፈልገው ነገር ዓረፍተ ነገር ጻፍ። | እንደ ዛሬው ዓይነት የአየር ሁኔታ ከቤት ውጭ መቆየት የሚችሉ የአምስት እንስሳዎችን ስእል ሳል። ለእያንዳንዱ እንስሳ ይህን ዓይነት የአየር ሁኔታ እንዲቋቋምይ የሚስችላቸው አንድ የሰውነት ገጽታ ጥቀስ። | ከመጽሓፍ ውስጥ አንድ ስሜቱን የሚገልጽ ገጸ ባህርይ ምረጥ። እንዴት ነው የተሰማው? ይህ ስሜት እንዳላቸው ከመጽሓፉ ውስጥ የሚያሳይ ሁለት ዝርዝር ነገሮች ጻፍ። | በአንድ ሙዚቃ ዳንስ ፍጠር ከዛም ቤት ውስጥ ላለ ሰው ደንስለት። |
| | አማራ 24 ባለ 1 × 1-  ካሬ ጫማ ንጣፍ አላት፣ በዚህ ተጠቅማ አራት ማዕዘን የሆነውን መታጠብያ ቤትዋን ማንጠፍ ፈለገች። የመታጠብያ ቤቱ ልኬት ምን ያህል ሊሆን ይችላል? እንዴት አወቅ? | ከታሪክ ስለ ምታደንቀው አንድ ሰብ አስብ። ለዛ ሰው ክብር ስለ ሚከበር በዓል ጻፍ። | በእያንዳዱ 4 ወቅቶች የምታደርገውን ነገር የሚያሳው ስእል ሳል። በእያንዳንዱ ስእል አንድ ዛፍ አስገባ፣ በዛ ወቅት የሚለበስ ልብስ ለብሰህ የሚያሳይ ስእልም አካትት። | Clever ላይ ወደ PebbleGo ግባ። ስለ አንድ አዲስ ሰው የህይወት ታሪክ አንብብ። ዋና ዋና ሓሳቦችንናን ስለዛ ሰው አስፈላጊ ዝርዝሮች ማስታወሻ ጻፍ። | የምትወደውን መዝሙር እየዘመርክ በግሮችህ ጣት ቁም። |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 120-75=______ የዚህን ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ጻፍ። በተቻለህ መጠን ትክክለኛውን መልስ የሚያሳይ ብዙ ዓረፍተ ነገሮች ጻፍ። | የቤትህን የምትኖርበትን አከባቢ የሚያሳይ ካርታ ሳል። ኮምፓስ አካትት እንዲሁም ምልክቶችንና ቀለሞችን የምትገልጽበት ቁልፍ ቃል ተጠቀም። | ውሃ ውስጥ የሚሟሙ ሶስት የምግብ ዓይነቶች (ቅመማ ቅመም፣ ዱቄት፣ ስኳር፣ ጭው፣ ካካዋ የመሳሰሉት) እንዲሁም ውሃ ውስጥ የማይሟሙ ሶስት የምግብ ዓይነቶች ተጠቅመህ ሙከራ አካሂድ። ምን እንዳደረክና ግኝቶችን መዝግብ። | Clever ላይ ወደ Visit World Book ግባ። አሳተፊ የሆነውን ካርታ ተጠቅመህ ከዚህ ቀደም ሄደህበት የማታውቀውን ከተማ ጎብኝ። ዋና ዋና ሓሳቦችንናን ስለ ቦታው አስፈላጊ ዝርዝሮች ማስታወሻ ጻፍ። | ከበላሃቸው እያንዳንዱ የምግብ ዓይነት አራት ምግቦች ጻፍ፦ ፍራፍሬ፣ አትክልት፣ ፕሮቲኖች፣ የወተት ተዋጽኦ እንዲሁም ጥራጥሬ።. |